# አገሬን ምን ነካው?

አብርሃም በየነ

ሞተ-በፈቃዱ አይሉት አስከሬን
እምቢታ የሸሸው ምን ነካው አገሬን?

ድሮ ድሮ ጥንታዊት አገሬ የአፍሪቃ የዳቦ ቅርጫት ትባል ነበር። በነጻነት ቀናኢነቷ የጥቁር ህዝብ የአርነት አርማም ነበረች። ክብሯ ደርዝ ነበረው። ታሪኳም ገናና ነበር።

ሕዝቧ ጠግቦ አዳሪ፣ ድንበሯ ተፈሪ፣ ዝናዋ በዓለም እውቅና የተቸረው አገር ነበረች። የዕምነቷ ቅላጼ በቅዱስ መጽሐፍ አርባ ጊዜ ስሟን ያስጠቀሰ ቅድስና ነበረው። ጥንታዊት ኢትዮጵያ በጅግንነቷ ተፈርታ፣ በሃብቷ ኮርታ፣ በዕምነቷ ፀንታ፣ የዜጎቿ በጎ ምግባር ትምሳሌነቱ ለሰው ዘር ሁሉ ትውፊት የነበረው አገር ነበረች።

መሪዎቿ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው፣ መንግሥታቸውን ሰሌን ሠርተው የሚያስተዳድሩ፣ ሕዝባቸውን በፍቅራ ይመሩ የነበሩ ፃድቅ ስለነበሩ ፃዲቁ ዮሐንስ ይባሉ ነበር። ጥንታዊት ኢትዮጵያ ቄስ በመስቀሉ፣ መእመን በቃሉ፣ ታቦት በመንበሩ፣ ሕዝብ በምግባሩ፣ ፀንቶ ይኖር ዘንድ የህግ አምላክ የነበራት አገር ነበረች። ተበዳዩ ዜጋ ጨርቁን በበዳዩ ጨርቅ ቋጥሮ በህግ አምላክ ካለው እግሩን የማይነቅልባት አገር ነበረች።

የድሮዋ ኢትዮጵያ መናኒያን በበርሃ ቅጠል ሸምጥጠው፣ ባህታዊያን በገዳም ቤት ዘግተው፣ መነኮሳት መቋሚያ ተመርኩዘው፣ አረጋዊያን ዳዊት ደግመው፣ ምዕመናን በፀሎትና በምለላ፣ ነገስታት በመላ፣ ጀግኖች በጋሻ፣ ገበሬዎች በማረሻ፣ ታድገው ያቆዩአት አገር ነበረች።

አቡነ ተክለሃይማኖት ባንድ እግር ቆመው ደረቅ ባቄላ ቆርጥመው፣ አቡነ ጴጥሮስ አጥንት ከስክሰው በጌታ ምህረት ከጥፋት የታደጓት አገር ነበረች።

ይህች አገር ዛሬ ዕምነቷ ላልቶ፣ ቋጻሳቷ ወስልተው፣ ቀኖናዋ ተጥሶ፣ ዶግማዋ ተቃውሶ፣ ቤተ መቅደሷ እረክሶ፣ መካነ መንበሯ ቆነጃጅት የሚመላለሱበት ሳሎን ሆኗል።

የፀሎት ቤቷ ወደ ንግድ ቤት ተቀይሮ ቋጻሳቷ የምድሪቱ ቱጃሮች ሆነዋል። በመስቀሉ ፋንታ ሽጉጥ፣ በዕምነቱ ፋንታ ሽፍጥ አንግበው ትህትናን በንቀት ያራከሱና ትምክህትን በልቅና ያነገሱ መሪዎች ተሹመውባታል።

የዛሬዋ ቤተክርስቲያን ድሆቿን ንቃ፣ ዕምነቷን ፍቃ፣ ገዳማቷን እያቃጠለች፣ መናኒያኗን እያፈናቀለች በስኳር ንግድ መሪዎቿን የተዋጣላቸው ነጋድራሶች በማድረግ ፈጣሪዋን አስቆጥታለች።

ቤተ-ክህነት በጎቿን የማይጠብቁ እረኞች በላይዋ ላይ ኮፍሳ ወንጌል ሳይሆን ወንጀል የምታስፋፋ "የእግዚአብሔር ቤት" ሆናለች። የዛሬይቱ ቤተ-ክህነት "ፓትሪያርኳ" ገዳይ፣ ጳጳሳቷ አስገዳይ፣ ቀሳውስቷም በዳይና ሃጢአተኞች ሆነዋል።

በቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስትያን የባህታዊ ህይዎት ቅስፋለች። በጎንደር አደባባይ ኢየሱስ በጎቿን በግፍ አስጨፍጭፋለች።

የበጎቿ ዕረኛ መሆኗ ቀርቶ የተኩላው ተባባሪ በመሆን በቅጥር ግቢዋ ከለላ የጠየቁትን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መጠለያ ነፍጋ በመትረየስ አሳጭዳለች።

በሺህ የሚቆጠሩ አማራዎች ከደቡብ ኢትዮጵያ ተፈናቅለው በግቢዋ መጠለያ ሲሹ እነዚህንም እንደ ተማሪዎቹ ደጇን ዘግታ ባዲስ አበባ ጎዳናዎች የፈሰሱ አሸዋ አድርጋቸዋለች።

መዲናችን አዲስ አበባ ከላይ ሆነው ሲያዩዋት ሰማይ ጠቀስ ፎቆቿና የውበት ለኸት የተቀቡት ቪላዎቿ በጨለማው ፍርግርግ መብራቷ ታጅበው ድሎትና ቅንጦት እንጂ በውስጧ ምንም የከፋ ነገር የሌለባት መድራዊ ገነት ትመስላለች።

ሀቁ ግን የድሆቿ ኤሎኼ በጠገቡት ሁካታ ተውጧል። የዜጎቿ መብት በአምባገነኖቿ ጫማ ተረግጧል። የርሃብተኞቹ ጠኔ በዲታዎቹ ጥጋብ ተሸፍኗል። የነዳያኑ መከራ በድሎተኞች ፈንጠዝያ ተቀብሯል። ለነዚህ ጎስቋላ ዜጋዎች ፀሀይ ብርሃኗን ነፍጋቸዋለች። የጨለማው ሰማይም ክዋክብቱን ሰውሮባቸዋል። ሰለሆነም ቀኑና ሌሊቱ ፈረቃው አይታወቃቸውም።

የመሪዎቹን ጥጋብና የድሆቹን በደል አይቶ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለቀሰላት እንደ ኢየሩሳሌም ከተማ አዲስ አበባም የሚያለቅስላት አምላክ አላደላት ይሆናል። እርሱን ሆነው ግን ስቅ ስቅ ብለው የሚያለቅሱላት ባህታዊያንና አማራዎች ሞልተው ተርፈዋታል።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ በፍትህ የተበደለች፣ በድህነት የነገሰች፣ በፍርሃት የተናጠች፣ የጀግና ነፍቆት ያነሆለላት፣ የበደል ዋንጫዋ ሞልቶ የተደፋባት አገር ሆናለች።

ድሮ ድሮ በርስትና በሚስት ዋዛ የለም ይል የነበረው ሕዝብ ዛሬ ዛሬ እርስቱንም ሚስቱንም ሲቀማ እምቢተኝነቱንም አብሮ የተቀማ ይመስላል። በቁሙ ሲቀብሩትም አሜን ብሎ ነው አፈር የሚለብሰው። ይህን የት የሌለ ባህርይ ስትታዘቡ አገሬን ምን ነካው? ትላላችሁ።

ስምን እናት ታወጣዋለች ይባላል። ነጋ ነወጠ ብላ። ስምና ግብር ሲመሳሰሉም የወላድ ማህፀን በድባቡ ይኑር ያሰኛል።

አፈሩ ይቅለላቸውና አጼ ሃይለስላሴ በአስራ ዘጠኝ ስድሳዎቹ መጀመሪያ ሰሜኑን ሱዳን ከደቡቡ ጋር ሲያስታርቁ እገረመንገዳቸውን ከካርቱም መሪዎች ጋር አንድ ውል ተዋውለው ተመለሱ።

ከደቡብ ሱዳን ከፊል መሬት ወደ ጋምቤላ ተሸጋሽጎ በምትኩም ከጎንደር ከፊል መሬት ወደ ሱዳን እንዲሄድ ተዋዋሉ። የውሉ ቋጠሮ አፈትልኮ ምስጢሩ ከመውጣቱ በፊት ፓርላማው እንዲነጋገርበት ሆነና ውይይቱ ጠብ አጫረ።

ጎንደሮች “በማን ኪሳራ ማን አትራፊ ይሆናል?” ሲሉ ስምምነቱን ተቃወሙ። የንጉሱ ደጋፊዎች ግን “መሬት ቢሄድ መሬት ነው የመጣው…” ሲሉ ተቃውሞውን ስለአቃለሉት ነገሩ  ከርሮ ወንበሮች ተጋጩ። የወንበሮቹ ግጭትም ወሬው ጎንደር ተሰማና አየሩን በጭንቀት ወጠረው።

አመሻሹ ላይ ነጋ ነወጠ ጓንዴውን ወልውሎ ትግሬ መጮሂያ( ገነት ተራራ) ወጣና አፈሙዙን ወደ ቤተመንግስቱ አዙሮ አየሩን በሶስት ጥይት አርሶ ፋኖነቱን አወጀ። ሌሊቱን የቀዳማዊ ሃይለስላሴ ሁለትኛ ደረጃ ት/ቤት ግቢ በተቃውሞ ወረቀት አሸብርቆ አደረ። ከዚያም የመማር ማስተማሩ ሂደት ተቋረጠ።

የተማሪው መሪ በጸጥታ ሃይሎች  በደረቁ መላጨቱ ተወራና የጎንደር ከተማ በሽብር ተናጠች። ንጉሱም የህዝቡን ቁጣ ሰምተው ሳይቃጠል በቅጠል ለማለት ይመስላል ስምምነቱን ሰረዙት።

ይህ ሁሉ የሆነው ድሮ ነው። ያ ትውልድ አፍላ እሸት ሳለ። ገበሬው በእርስትና በሚስት ዋዛ የለም ይል በነበረበት ዘመን። የተማሪው ማህበር መሬት ላራሹ ብሎ በተነሳበት ዘመን።

ሀይሉ ገብረ ዮሃንስ፣ አበበ ወርቁ፣ ጸጋየ ደብተራውና ዋለልኝ መኮንን ታገል ሲሉ የተበደለው ሰው ባቻ ሳይሆን ወተቱም ይሸፍት በነበረበት ዘመን።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ በደል አያስኮርፍም። ውርደትም አያሳፍርም። እርስትንና ሚስትን መነጠቅ ነውርነት የለውም። ዛሬ ሲገፉ ውሎ ቢያድር እንኳ ወተቱ ሰውም መሸፈትን አያልምም።

መሬቱም ለሱዳን ቢሰጥ እንደ ነጋ ነወጠ ጠመንጃ የሚመዝ ባለሃሞት ሰው የለም። ግብጾች፣ ቻይናዎች፣ ህንዶች፣ አረቦች፣ ኮሪያዎች፣……… ሌሎችም ሌሎችም ሰንትና ሰንት ኩዳድ መሬት ሲወስዱ ለምን? ብሎ የጠየቀ የለም።

የራያ መሬት በትግሬ ሲነጠቅ ዝም ነው። ፀለምት፣ ራስ ዳሽን፣ ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ሁመራና ዳንሻ ባለርስቶቹ  እየተፈናቀሉ ተግሬዎቹ ሲወርሱት ዝም ነው።

አማራዎች በበደኖ፣ በወተርና በአርባጉጉ በኦነግና በኦሂዴድ ካደሬዎች ከነነፍሳቸው በገደል ሲወረወሩ ዝም ነው። ከአሶሳ ተፈናቅለው ጎጃም በርሃ ላይ ሲደፉ ዝም ነው።

ክርስቲያኖች በደቡብና በደቡብ ምእራብ ቤተክርስቲያኖቻቸው እየተቃጠሉ ምዕመናኑም ወደ ቋያው ከነነፍሳቸው ሲወረወሩ ዝም ነው።

አሰቦት ገዳም ሲቃጠል ዝም። የዋልደባ ገዳም ሲፈራርስ ዝም። ከሰባ አመስት ሺህ በላይ ቁጥር ያላቸው አማራዎች ከደቡብ ግዛቶች ሲባረሩ ዝም። እነዚህ ስደተኞች በቅድስት ስላሴ አጥር ግቢ  እንዳይጥለሉ ሲባረሩ ዝም ነው።

በዛሬዋ ኢትዮጵያ የበደል ዋንጫ ሞልቶ ሲደፋ እንደ ድሮው ቁጣና አመፅ ሳይሆን ምላሹ ዝምታ ሆኗል።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከአማራና ከአማርኛ ቋንቋ ጋር ተዳብለው የዘር ማጥፋት ወንጀል ሲፈፀምባቸው ምሁሩም ዝም። ተማሪውም ዝም። ገበሬውም ዝም። ሁሉም ዝም። አገሬን ምን ነካው?

በዝምታው ውስጥ ግን የቂም እሳት ተድፍኗል። ሕዝባችን እንዳይጮህ ታፍኗል። አንድ እንዳይሆን በዘር ተከፋፍሏል። አመጽ እንዳያነሳ ክንዱ ዝሏል። ከሁሉም በላይ ግን እንዳይኖር “ተገድሏል። ግና ግና መቃብሩን ፈንቅሎ የሚነሳበት ቀን ዕሩቅ ስለማይሆን ሀዘናችን ለሚቼ ሳይሆን ለገዳዩ ነው። ለምን? ቢባል ዕዳውን እስከ ወለዱ መሰብሰብ ይከብደዋልና!

ሚያዚያ 2004

………………………………………..//………………………………………..